በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.239814

ጥቅምት 07/2016 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካቾች፡

1. ሚሲስ ቬሬና በክሪ
2. አቶ አሚን በክሪ
3. ወ/ሮ አይዳ በክሪ
4. ወ/ሮ ሊዲያ በክሪ
5. ወ/ሮ ዮብዳር በክሪ

ጠ.አቶ ዮሐንስ አይገፉ - ቀረቡ

ተጠሪ፡ ሲስተር ሙኒራ በክሪ - ጠ አቶ ኃ/ማሪያም - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ ኑዛዜ ይፍረስልኝ በሚል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/296155 ላይ ህዳር 29/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካቾችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ ያደረገበትን ብይን በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ ግንቦት 02/2014 ዓ.ም ፅፈው በአሁን አመልካቾች ላይ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱም ጭብጥ የግራ ቀኙ ወላጅ አባት የሆኑት የሟች ዶ/ር በክሪ አብዱላሂ ቱኑ ወራሽ መሆናቸውን በፍርድ ቤት ያረጋገጡ መሆኑን፤ ሟች አባታቸው ጥቅምት 09 ቀን 2011 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ተጠሪን በዝምታ ከውርስ በመንቀል ጠቅላላ ንብረታቸውን ለአሁን አመልካቾች የተናዘዙ መሆኑን በመግለፅ ኑዛዜው ፈራሽ ነው እንዲባልላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት የአሁን አመልካቾች ግንቦት 09/2014 ዓ.ም የተፃፈ የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና አማራጭ የስረ ነገር ክርክር አቅርበዋል፡፡ የመቃወሚያው ይዘትም የውርስ ሀብት ክፍፍሉን አስመልክቶ ግራ ቀኛችን ሐምሌ 16 ቀን 2013 ዓ.ም በተደረገ ስምምነት የጨረስን በመሆኑ ክሱ በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ ነው፤ ክሱም የፍ/ብ/ህ/ቁ/874(3) እና 973 በሚያዘው መሰረት በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ያልቀረበ በመሆኑ በይርጋ ይታገዳል የሚል ነው፡፡ ፍሬ ጉዳዩን በተመለከተ ደግሞ ሟች ሰኔ 02 ቀን 2007 ዓ.ም ለአሁን ተጠሪ እንዲሁም ጥቅምት 09 ቀን 2011 ዓ.ም ለአሁን አመልካቾች በሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ ፅ/ቤት የተመዘገቡ ሁለት ኑዛዜዎች ያደረጉ በመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁ/895 በሚፈቅደው መሰረት ሁለቱ ኑዛዜዎች ጎን ለጎን ተፈፃሚ ከሚደረጉ በስተቀር የሚሻርበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት የአሁን አመልካቾች ከውርስ ሀብቱ ክፍፍል ጋር በተያያዘ ተፈፅሟል የሚሉት የዕርቅ ስምምነት የፍ/ብ/ህ/ቁ/3318 እና 3325 መስፈርትን የማያሟላ እና በፍ/ብ/ህ/ቁ/277 መሰረትም በፍ/ቤት ቀርቦ የተመዘገበ ባለመሆኑ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ/244(1)(ረ) መሰረት በመቃወሚያነት ሊቀርብ የሚችልበት የህግ አግባብ የለም፤ የይርጋ መቃወሚያውን በተመለከተ የፍ/ብ/ህ/ቁ/974(3) ተግባራዊ የሚሆነው ከመንፈስ መጫን ጋር ለተያያዘ ክርክር ነው፤ የፍ/ብ/ህ/ቁ/973 ደግሞ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ከኑዛዜ ፎርም እና ህጋዊነት ጋር ለተያያዘ ክርክር ነው፤ ይልቁንም በዚህ ረገድ ተግባራዊ ሊሆን የሚገባው በፍ/ብ/ህ/ቁ/1123 ላይ የተመለከተው የ2 አመት እና የ10 አመት ይርጋ ስለመሆኑ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/152134 አስገዳጅ የህግ ትርጉም የሰጠበት በመሆኑ የይርጋ መቃወሚያው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡

የክሱን ፍሬ ነገር ክርክርንም በተመለከተ ምንም እንኳን ሟች ሰኔ 02 ቀን 2007 ዓ.ም በተደረገ ኑዛዜ በቂርቆስ ክ/ከተማ የሚገኘውን የቤት ቁጥሩ 416 የሆነ መኖሪያ ቤት እና በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኙ አክሲዮኖችን ለተጠሪ የተናዘዙ ቢሆንም ሟች ዘግይተው ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ማንኛውንም በስማቸው ተመዝግቦ የሚገኝ የሚንቀሳቀስም ሆነ የማይንቀሳቀስ ንብረት እና አክሲዮን ለአመልካቾች መናዘዛቸውን የገለፁ በመሆኑና ሁለቱን ኑዛዜዎች ጎን ለጎን ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፤ ኑዛዜዎቹን በአንድነት ተፈፃሚ ማድረግ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የኋላኛው ኑዛዜ የአሁን ተጠሪን በዝምታ ከውርስ የነቀለ በመሆኑ ሟች ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ለአሁን አመልካቾች ያደረጉት ኑዛዜ በፍ/ብ/ህ/ቁ/938 እና 939(2) መሰረት ፈራሽ ነው በማለት ውስኗል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አመልካቾች ይህንን ውሳኔ እና ቀደም ሲል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያን አስምልክቶ የተሰጠውን ብይን በመቃወም ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታ ያቀረቡ ቢሆንም ፍርድ ቤቱ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 337 መሰረት ይግባኙን ዘግቷል፡፡

የአሁን ሰበር አቤቱታ የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካቾች ጥር 01/2015 ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ብይን ላይ ተፈፅሟል ያሏቸውን መሰረታዊ የህግ ስህተተ ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም ያቀረብነው የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ ከህግ አግባብ ውጭ ታልፎብናል፤ ሟች ሰኔ 02/2007 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ለተጠሪ ቤት እና አክሲዮን ሰጥተዋል፤ ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ደግሞ ቀድሞ በተደረገው ኑዛዜ ለተጠሪ ከተሰጡት ንብረቶች ውጭ ያሉትን ጠቅላላ ንብረታቸውን ለአመልካቾች አስተላልፈዋል፤ እነዚህ ሁለቱ ኑዛዜዎች ጎን ለጎን ሊፈፀሙ የሚችሉ ናቸው፤ የሁለቱን ኑዛዜዎች አፈጻፀም አስምልክቶም ግራ ቀኛችን ሓምሌ 16/2013 ዓ.ም ስምምነት የተፈራረምን በመሆኑ እና ስምምነቱ በመካከላችን እንደ ህግ የሚቆጠር በመሆኑ ተጠሪ በስምምነቱ መሰረት እንዲፈፀም ከሚጠየቁ በቀር ክስ ሊቀርብበት አይችልም፤ የኑዛዜዎቹ ይዘት እና አፈፃፀም በዚህ መልኩ ሊተረጎምን ሲገባ የስር ፍርድ ቤቶች ይህንን ወደ ጎን ትተው ሁለቱ ኑዛዜዎች ጎን ለጎን ሊፈፀሙ አይችሉም ማለታቸው የኑዛዜዎቹን ተግባራዊ አውድ እና አዎንታዊ የህግ አተረጓጎምን ያልተከተለ በመሆኑ የተሰጠው ውሳኔ እና ብይን ውድቅ ተደርጎ ባቀረብነው የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ መሰረት ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል ነው፡፡

አቤቱታው በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ክሱ መቅረብ የነበረበት ግራ ቀኙ ሐምሌ 16/2013 ዓ.ም በተፈራረሙት ስምምነት መሰረት አልያም አሁን በቀረበበት ዓይነት የመሆኑ ጉዳይ ለዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ተጠሪ መልስ እንዲጡበት ተደርጓል፡፡

በዚሁ መሰረት ተጠሪ የካቲት 06/2015 ዓ.ም የተፃፈ መልስ አቅርበዋል፡፡ መሰረታዊ ይዘቱም ሟች ሰኔ 02/2007 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ቤት እና አክሲዮን የተናዘዙልኝ ቢሆንም ቤቱን በህይወት እያሉ የሸጡት እና አክሲዮኑንም ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ባደረጉት ኑዛዜ ለአመልካቾች በኑዛዜ አስተላልፈው የቀደመው ኑዛዜ ቀሪ በመሆኑ በሌለ ኑዛዜ ላይ ስምምነት የምናደርግበት አግባብ የለም፤ ተደረገ የተባለው ስምምነትም ቢሆን አመልካቾች ከውጭ ሀገር መጥተው አጠቃላይ የውርስ ክፍፍል እስኪደረግ ድረስ በሚል የተፈረመ መግባቢያ ሰነድ(Memorandum of Understanding) እንጂ አስገዳጅ ውል ባለመሆኑ ክስ የቀረበበት ጉዳይ በስምምነት ያለቀ ነው ሊባል አይችልም፤ ይርጋን አስምልክቶም ለመቃወሚያው መሰረት የሆኑት የፍ/ብ/ህግ ቁጥር 874 እና 973 ሲሆኑ እነዚህ ድንጋጌች ለቀረበው ጉዳይ አግባብነት የሌላቸው በመሆኑ ሁለቱም መቃወሚያዎች ውድቅ መደረጋቸው በአግባቡ ነው፤ የኑዛዜዎቹን ይዘት አስምልክቶም የቀደመው ኑዛዜ ቀሪ የተደረገ እና ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም በተደረገው ኑዛዜ ውስጥ ተጠሪ ያልተካተቱ በመሆኑ ኑዛዜው ተጠሪን በዝምታ ከውርስ የነቀለ ነው፤ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤቶች ኑዛዜው ሊሻር ይገበዋል በሚል በሰጡት ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ህተት ባለመኖሩ ሊፀና ይገባል የሚል ነው፡፡ አመልካቾችም የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክ የመልስ መልስ በማቅረብ ሞግተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም ጉዳዩን መርምሯል፡፡ በዚሁ መሰረት የአሁን አመልካቾች ክስ የቀረበበት ጉዳይ በእርቅ ስምምነት ያለቀ በመሆኑ ክስ ሊቀርብበት አይገባም በማለት ያቀረቡት የመጀመሪያ ደረጃ የክስ መቃወሚያ የመታለፉ አግባብነት በቅድሚያ ሊመረመር የሚገባው ጉዳይ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ይህንኑ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ነጥብም ከግራ ቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

የአሁን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ሟች አባታቸው ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ያደረጉት ኑዛዜ በዝምታ ከውርስ የነቀላቸው መሆኑን ጠቅሰው ኑዛዜው በፍርድ ቤት ውሳኔ ፈራሽ ነው እንዲባልላቸው ነው፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው ሟች ሰኔ 02/2007 ዓ.ም ባተረፉት ኑዛዜ ለተጠሪ ንብረት ያወረሱ እንዲሁም ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ባተረፉት ኑዛዜ ደግሞ ለአመልካቾች ንብረት ያወረሱ በመሆኑ ተጠሪ ከውርስ ተነቅያለሁ ሊሉ አይገባም፤ የሁለቱን ኑዛዜዎች አፈፃፀም አስመልክቶም ግራ ቀኛችን ሐምሌ 16/2013 ዓ.ም በተፃፈ የእርቅ ስምምነት የተጠናቀቀ በመሆኑና ክሱም በእርቅ ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

እንግዲህ አንድ የቀረበ ክርክር አልያም ወደፊት የክርክር ምንክያት ሊሆን ይችላል ተብሎ የሚገመትን ጉዳይ በእቅር ስምምነት/ግልግል/ መቋጨት በህግም የተፈቀደ ጉዳይ ነው፡፡ ተከራካሪ ወገኖች በመካከላቸዉ የተፈጠረዉን ወይም ወደፊት ሊፈጠር የሚችለዉን ክርክር በግልግል ሊያስቀሩ ስለሚችሉበት ሁኔታ እንዲሁም የግልግል ሂደቱም ስለሚመራበት ስርዓት በፍ/ብ/ሕ/ቁ.3307 እና ተከታዮቹ ድንጋጌዎች በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ በዚሁ ስርዓት መሰረት ተከራካሪ ወገኖች ጉዳያቸውን በእርቅ ስምምነት ጨርሰው ከሆነ አልያም ጉዳዩ ለእርቅ ተቀጥሮ ከሆነ በዚያው ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንደማይችሉ፤ ክሱ ቀርቦ ከሆኑ ሌላኛው ተከራካሪ ወገን ይህንኑ ሁኔታ ጠቅሶ ክሱን ሊቃወም እንዲሚችል የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 244/2/ረ/ ይደነግጋል፡፡ በፍርድ ቤት ክስ የቀረበበት ጉዳይ በሽምግልና ታይቶ በስምምነት የተፈጸመ መሆኑን ወይም ለእርቅ የተቀጠረ መሆኑን የሚያረጋግጥ ተጨባጭ ማስረጃ ሲቀርብ ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤት ክሱን ውድቅ በማድረግ መዝገቡን መዝጋት የሚገባው ስለመሆኑ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ.245(2) ይደነግጋል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ሟች ሰኔ 02/2007 ዓ.ም እንዲሁም ጥቅምት 09/2011 ዓ.ም ለግራ ቀኙ ያደረጉትን ኑዛዜ አስመልክቶ ግራ ቀኙ ሐምሌ 16/2013 ዓ.ም ስምምነት መፈራረማቸውን ተጠሪም የካዱት ጉዳይ አይደለም፡፡ ተጠሪ ስምምነቱ መኖሩን ሳይክዱ እያቀረቡ ያሉት መከራከሪያ ስምምነቱ የአሁን አመልካቾች ከውጭ ሀገር ሲመለሱ የውርስ ክፍፍሉ ስለሚመራበት ሁኔታ የተደረገ መግባቢያ ሰነድ እንጂ ገዝር ውል አይደለም የሚል ነው፡፡ በእርግጥ የተባለው ሰነድ አርዕስቱ መግባቢያ ሰነድ በሚል የተገለፀ መሆኑን አጣሪ ችሎት ከባለጉዳዮች ተቀብሎ ከመዝገብ ካያያዘው የውሉ ሰነድ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም አጠቃላይ የሰነዱ ይዘት ሲፈተሽ የስምምነቱ ጉዳይ የሁለቱን ኑዛዜዎች አፈፃፀም አስመልክቶ የተደረገ መሆኑን፤ ሟች ቀድሞ ባደረጉት ኑዛዜ በቂርቆስ ክ/ከተማ የሚገኘውን መኖሪያ ቤታቸውን ለተጠሪ በኑዛዜ ሰጥተው የነበረ ቢሆንም ቤቱ አሁን ላይ ባለመኖሩ በዚያ ምትክ ተጠሪ ከውርስ ሀብቱ ላይ ሊያገኙ ስለሚገባቸ ድርሻ በዝርዝር የያዘ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ስምምነቱ በግራ ቀኙ መካከል መብት እና ግዴታን የሚፈጥር አስገዳጅ ስምምነት መሆኑን የሚያረጋገጥ እንጂ ተራ መግባቢያ ሰነድ የሚባል አይደለም፡፡ ከስምምነት ሰነዱ ይዘት አኳያም ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ አስቀድሞ በስምምት ያለቀ መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው፡፡ አንድ ጉዳይ አስቀድሞ በስምምነት አልያም በሽምግልና ከተጠናቀቀ በዚያው ጉዳይ ላይ በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ እንደማይቻል ከላይ ተመልክቷል፡፡ ጉዳዩ ይህ ሆኖ እያለ የስር ፍርድ ቤቶች ክስ የቀረበበት ጉዳይ በእርቅ አልቋል ለማለት አይቻልም በሚል ምክንያት በአመልካቾች በኩል የቀረበውን መቃወሚያ ውድቅ ማድረጋቸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 244(2)፣(ረ) ድንጋጌን ይዘትና መሰረታዊ ዓላማ ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

## ውሳኔ

1. የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/129291 ላይ ሐምሌ 21/2014 ዓ.ም የሰጠው ብይን እንዲሁም በዚሁ መዝገብ ቁጥር ላይ ነሓሴ 27/2014 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፣ ይህንኑ በማጽናት የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ/296155 ህዳር 29/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ብይን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. ተጠሪ ክስ ያቀረቡበት ጉዳይ አስቀድሞ ግራ ቀኙ ሐምሌ 16/2013 ዓ.ም በተፈራረሙት የእርቅ ስምምነት በስምምነት ባለቀ ጉዳይ ላይ የቀረበ በመሆኑ በፍ/ብሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 244/2/ረ/ መሰረት ውድቅ ተደርጓል፡፡

## ትእዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !